# ይድረስ ለክቡር አቶ በረከት ስምዖን

# የበለጠ መረጃና ማብራሪያ ሊሰጠው የሚገባው የግብፅ ሕዝብ ነው

(ከአብዱራህማን አህመዲን - የቀድሞ የፓርላማ አባል)

*(ይህ ጽሁፍ በሰንደቅ ጋዜጣ 8ኛ ዓመት ቁጥር 406 የሰኔ 12 ቀን 2005 ዓ.ም እትም ቀርቧል፡፡ ለመወያያ ይጠቅማል በሚል መንፈስ በአይጋ ፎረም እንዲቀርብ ተልኳል)*

አንዳንድ ጊዜ ሁሉም ነገር ስልችት ይለኝና "ምናለ አሁን አርፌ ብቀመጥ" የሚል ስሜት ያድርብኛል፡፡ እንዲህ ያለው ስሜት ተራ ሽንፈት መሆኑን ስረዳ ደግሞ እንዲህ እንደ አሁኑ እመር ብዬ ብዕሬን አነሳለሁ፡፡ እኔ ተራ ሀገር ወዳድ ነኝ፡፡ ለሀገሬ ያለኝ ፍቅር ወሰን ያጣ መሆኑንም እረዳለሁ፡፡ እናም፣ አሁን አሁን ይሄ አለቅጥ አገሬን መውደዴ "እጥፊዬ ይሆን እንዴ?" የሚል ጥያቄ እያጫረብኝ መጥቷል፡፡ ... ሰሞኑን ከወደ ግብፅ እየሆነ ያለውን "እብደት" መሰል ነገር ስሰማ "ተራ የአገር ወዳድነት" ስሜቴ ተቀሰቀሰና እነሆ ይህቺን ማስታወሻ ለመክተብ ተነሳሁ፡፡

የጽሑፌን ርዕስ ለክቡር አቶ በረከት ስምዖን እንዲሆን ማድረጌ አለምክንያት አደለም፡፡ እርሳቸው የሚመሩት ተቋም "የመንግስት ቃል አቀባይነት" ሚና ያለው በመሆኑና በግብፅ ፖለቲከኞች የተቀሰቀሰብንን "የሥነ-ልቦና ጦርነት" ለመመከት ቀዳሚውን ሚና መጫወት የሚገባቸው እርሳቸውና እርሳቸው በሚመሩት ተቋም ስር ያሉ ሌሎች ተቋማት በመሆናቸው ነው፡፡

ክቡር አቶ በረከት፣ በቅድሚያ የናፍቆቴን ያህል እንደምን አሉ? እኔ እንዳለሁ አለሁ፡፡ ክቡር ሆይ! ይህቺን ጦማር በሰንደቅ ጋዜጣ በኩል እንድጽፍልዎ ግድ ያለኝ፣ ሰሞኑን በግብፅ ፖለቲከኞች እየተባለ ያለውና በእኛ በኩል እየተሰጠ ያለው የአጸፋ ምላሽ አላረካኝ ስላለ 'እንዲህ ቢሆንስ' የሚል ሃሳቤን ለመሰንዘር በማሰብ ነው፡፡

ክቡር ሆይ! በርግጥ እርስዎ እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዓርብ እለት በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የነበራችሁን ቆይታ ከሞላ ጎደል ተከታትያለሁ፡፡ እንደዚያ ያለው ማብራሪያ የግድቡ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቃሚ ግንዛቤ እንደሚሰጥ እገነዘባለሁ፣ አምናለሁም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከዚሁ ጎን ለጎን አማርኛ ለማይችለው ለግብፅ ሕዝብም አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት የግብፅ ፖለቲከኞች ያጎበጡትን አመለካከት ማቃናት በዚያው ልክ አስፈላጊ መሆኑ ይታየኛል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ለመገንባት ሲነሱ ከማን ምን አሉታዊ ሁኔታ ሊመጣ እንደሚችል ቀድመው ገምግመውና አስበውበት የጀመሩት ሥራ በመሆኑ የግብፅ ፖለቲከኞች ጩኸት ሊያስበረግጋቸው አልቻለም፣ አይችልምም፡፡ እናም ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ በመቁጠር አሁንም ተረጋግተው ሥራቸውን በመስራት ላይ ናቸው፡፡ ወደፊትም ከዚህ ተግባራቸው ንቅንቅ የሚያደርጋቸው ምድራዊ ኃይል እንደማይኖር አምናለሁ፡፡ እናም

በኢትዮጵያ በኩል የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት መረጃና ማብራሪያ ሊሰጠው የሚገባው የግብፅ ሕዝብ እንደሆነ ይታየኛል፡፡ ይህንን የምልበት ምክንያት አለኝ፡፡

እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት የግብፅ መንግስትና ፖለቲካ በተረጋጋ ሁኔታ ላይ አይገኙም፡፡ እናም ይህንን የውስጥ ችግራቸውን ለማርገብ ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ የሕዝባቸውን ስሜት የሚቀሰቅሱ ውጫዊ ሁኔታዎችን በማራገብ አቅጣጫ ማስቀየር እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የግብፅ አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሀራቸው ፖለቲኞች በሚነግሯቸው "ቅጥፈት" ተወናብደው በግብፅ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ እስከ መውረር መሄዳቸውን ሰምተናል፡፡ የግብፅ ፖለቲከኞች እንደዚያ ዓይነት ነውረኛ ነገር በእኛ ኤምባሲ ላይ እንዲፈጸም ሲያስደርጉ እዚህ አዲስ አበባ ላይ ኤምባሲ ያላቸው መሆኑን እንኳ ያሰቡበት አይመስለኝም፡፡

እንዲህ ያለው የግብፅ ፖለቲከኞች ግብታዊ እርምጃ ከአያቶቻቸውና ከቅድመ አያቶቻቸው (ከእነ እስማኤል ፓሻ) አለመማራቸውን ብቻ ሳይሆን፤ እጃችን በሶ ጨብጦ ሊጠብቃቸው እንደማይችል መገመት አለመቻላቸውንም ጭምር የሚያመላክት ነው፡፡ መቼም ጠጠር ሲወረውሩብን ቋጥኝ እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁ ኖሮ እንደዚያ ዓይነት "የጀበና ድንፋታ" እና ቀረርቶ ውስጥ ባልገቡ ነበር፡፡ በርግጥ በእኛ በኩል የሰከነ ሁኔታ ያለ በመሆኑ እነሱ በሄዱበት መንገድ አልተጓዝንም፡፡ እናም እንዲህ ዓይነቱ የእብደት መንገድ እንዳይደገም መምከር፣ ማስተማርና መረጃ መስጠት ይኖርብናል፡፡

ስለሆነም፤ ፖለቲከኞቹን እንተዋቸውና ምን እየሰራን እንደሆነ የግብፅ ሕዝብ እንዲያውቅ እናድርግ፡፡ እኛ የምንሰራው ግድብ የግብፅን ሕዝብ ሕይወት የማያናጋና ምንም ዓይነት አሉታዊ ሁኔታ የማይፈጥር መሆኑን "በሚገባቸው ቋንቋ" እናስረዳ፡፡ የሚገባቸው ቋንቋ ደግሞ ዐረብኛ ነው፡፡ የዐረብኛ ቋንቋን አቀላጥፈው የሚናገሩ ኢትዮጵያውያንም በርካታ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትም እሳት የበሉ ወጣትና አንጋፋ የዐረብኛ ቋንቋ ጋዜጠኞች አሉት፡፡ ይሁን እንጂ፣ የግብፅን ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ትክክለኛውን መረጃ በማቅረብ ለሁላችንም የሚበጀውን መንገድ በማመላከት እንደ እኛው ተረጋግቶ ስራውን እንዲሰራ ለማድረግ በየእለቱ ለግማሽ ሰዓት ያህል የሚሰራጨው የዐረብኛ ፕሮግራም በቂ ሊሆን አይችልም፡፡

ክቡር አቶ በረከት! የዐረብኛ ፕሮግራሙን በተመለከተ ያለኝን ሃሳብ ከማቅረቤ በፊት የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን በተመለከተ አንድ ነገር ለማለት እወዳለሁ፡፡ በኔ ግምት ባለፉት 22 ዓመታት ኢህአዴግን ሊዋጣለት ካልቻሉት ነገሮች አንዱ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን ማደራጀትና ለወቅቱ በሚመጥን ቁመና ለመምራት አለመቻሉ ይመስለኛል፡፡

ይህ ተቋም ሕዝብን፣ መንግስትን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማገልገል እንዳለበት በመቋቋሚያ አዋጁ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ሦስቱንም ወገኖች በአግባቡ የሚያስደስት ሥራ እንዳልሰራ በድፍረት መናገር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ይህንን "ድፍረት የተሞላበት" ሃሳብ እውነተኝነት ለማስረዳት በርካታ ምሣሌዎችን እየጠቀስኩ ማብራራት አይገደኝም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜም ጉልበትም በከንቱ ላለማባከን ሁለት ትንንሽ አብነቶችን ብቻ ልጥቀስ፡፡

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በየዕለቱ ለግማሽ ሰዓት ያህል በዐረብኛ፣ በፈረንሳይኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ስለ ማዳበሪያ ስርጭት፣ ስለ ግብርና ኤክስቴንሽን፣ ስለ መስኖ ልማት፣ ስለ 20/80 የኮንዶሞኒየም ቤቶች ግንባታና ምዝገባ፣ ወዘተ. የሚያቀርባቸውን ዝግጅቶች አልፎ አልፎ

ተከታትያለሁ፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በዐረብኛ፣ በፈረንሳይኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማሰራጨት ለሕዝብ፣ ለመንግስትም ሆነ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ፋይዳ አለው? በግሌ ይህንን በተመለከተ ባወጣ ባወርድ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ እውነት ይሄ ሕዝብን፣ መንግስትንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማገልገል ነው ወይስ የሀብት ብክነት?

ሁለተኛውን ምሳሌ ለቅርብ፡፡ ሀሙስ እለት አንድነት ፓርቲ የሰጠውን መግለጫ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከሀሙስ ማታ ጀምሮ እየደጋገመ ዘግቧል፡፡ ዓርብ እለት ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ደግሞ ይህንኑ ዜና ከአዲስ አበባ መስተዳድር ቴሌቪዥን ስርጭት ተከታትያለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ "አንድነት ፓርቲ መንግስትን የዲፕሎማሲ ስራ አልሰራም፣ ግድቡን የአንድ ፓርቲ ጉዳይ አደረገው፣…" ወዘተ. የሚል መግለጫ ማውጣቱን ነው አጉልቶ የዘገበው፡፡ አዲስ ቴሌቪዥን ደግሞ "አንድነት ፓርቲ በሀገር ጉዳይ ከማንም እንደማይደራደር" መግለጹን የዶ/ር ነጋሦን ድምፅ ጭምር እያሰማ አዎንታዊ ዜና ነበር ያቀረበው፡፡

ሁለቱ ጣቢያዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ያን ያህል ሀራምባና ቆቦ የሆነ የዜና ዘገባ ያቀረቡት ለምንድነው? እንደዚያ ዓይነቱ የዜና አቀራረብ እውነት ማንንነው የሚጠቅመው? ሕዝብን? መንግስትን? ወይስ የፖለቲካ ፓርቲዎችን? በኔ እምነት፣ እንደዚያ ዓይነት የዜና አቀራረብ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የተሰጠውን ሕዝብን፣ መንግስትን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማገልገል ተልእኮ የሚያሳካለት አይመስለኝም፡፡

ይህንን ድርጅት እንዲመሩ 'የድርጅት ፍቅርና ታማኝነት' ያላቸውን ሰዎች ከባህር ዳር፣ ከመቀሌ ወይም ከሐዋሳ ማምጣት ውጤት ሊያስገኝ እንዳልቻለ ደጋግመን ያየነው ይመስለኛል፡፡ በኔ እምነት የተሻለ የሚሆነው የጋዜጠኛነትን ሙያና ሥነ-ምግባር በቅጡ የተገነዘበ፣ በዘርፉ የጠለቀ እውቀትና ልምድ ያለው፣ የመንግስትንና የሕዝብን ራዕይ ጠንቅቆ የተገነዘበና ይህንንም ራዕይ ለማሳካት ፅኑ እምነትና ቁርጠኛነት ያለውን ሰው መመደብ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ብሩሕ አእምሮ ያለው ሰው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን እንዲመራ ቢደረግ ጣቢያውን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሀገሮች ተወዳጅና ተደማጭ በማድረግ የተዋጣለት ሥራ መስራት እንደሚችል እገምታለሁ፡፡

ክቡር ሆይ! በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዙሪያ አስተያየት መስጠት የፈለግኩት የድርጅቱን አመራርና አሰራር በማጠናከር የግብፅ ፖለቲከኞች የሚያወርዱብንን ፕሮፓጋንዳ መመከት ብቻ ሳይሆን፤ እውነትና ሀቅ እኛ ጋር እስካለ ድረስ 'አጥቂ' የኢንፎርሜሽን ስርጭት ማድረግ ይቻላል በሚል መንፈስ ነው፡፡ እናም ወደ ዋናው የጽሁፌ ርዕሰ ጉዳይ ልመለስና የግብፆችን ፕሮፓጋንዳ እንዴት እንመክተው? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ያለኝን ሃሳብ በማቅረብ ሃሳቤን ላጠቃል፡፡

እነ ጋዜጠኛ ታደሰ ሚዛን በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚያቀርቡት "የሚዲያ ዳሰሳ" እና በFM ሬዲዮ የሚቀርብ ማብራሪያና ትንተና ለሕዝባችን ግንዛቤ በመስጠት ተረጋግቶ ሥራውን እንዲሰራ ያደርገው እንደሆነ እንጂ የግብፆችን ፕሮፓጋንዳ በመመከት ረገድ ፋይዳ ያለው መስሎ አይታየኝም፡፡ ምክንያቱም ግብፆች አማርኛ አይሰሙም፡፡ የተሻለ የሚሆነው ክልሎች በአገር ውስጥ ቋንቋዎች ማሰራጨታቸውን እንዲቀጥሉ ቢደረግና የፌዴራል መንግስት የሚመራው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በሀገሪቱ የሥራ ቋንቋ እና በዐረብኛ፣ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ፕሮግራሞችን ሰፋ ባለ ጊዜና የአየር ሰዓት እንዲያሰራጭ ማድረግ ነው፡፡

ለግብፅ ሕዝብ እና ዐረብኛ ቋንቋ ለሚችሉ/ለሚሰሙ ሕዝቦች ብቻ ሃሳባችንን ማሰራጨቱ በቂ አደለም፡፡ እናም በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ጭምር ፕሮግራሞችን ማሰራጨቱ የበለጠ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህም የሥርጭት ሂደት በርካታ አጋሮችን እንደሚፈጥርልን ጥርጥር የለውም፡፡ በሦስቱ ዓለም አቀፍ ቋኗዎች የሚደረጉ ስርጭቶች ሌሎች ጎረቤቶቻችን ጭምር ሀሳባችንን ተረድተው ከስጋት ነፃ ስለሚሆኑ አጋርነታቸው የበለጠ ይጠነክራል፡፡ ሀቁን ሲረዱ ብድርና እርዳታ የከለከሉን ወገኖች መቀነት ሊፈታ፣ ካዝናቸው ሊከፈት እንደሚችልም መገመት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለዚሁ የፕሮፓጋንዳ ስራ ሲባል የኢትዮጵያ ምሁራን የሚሳተፉበት ዌብሳይት በዐረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ቢከፈትም መልካም ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች (በተለምዶ አጠራር ዲያስፖራዎች) በየዌብሳይቱ የሚያዘንቡትን  አሉባልታና ዋዛ ፈዛዛ ገታ አድርገው የተቃጣብንን የሥነ ልቡና ጦርነት ለመመከት ቢንቀሳቀሱ መልካም ነው፡፡ ዝም ብሎ 'የቤት መስሪያ ቦታ ይሰጠን፣ ለኮንዶሚኒየም ቤት መዝግቡን፣ ከቀረጥ ነፃ ይፈቀድልን፣ ፖሊሲ ይውጣልን፣...' ምናምን ማለት ብቻ በቂ አደለም፡፡ ፈረንጆቹ እንደሚሉት "There is no free Lunch!" የቁርጥ ቀን ሲመጣ ጋሻም፣ ጦርም፣ አንካሴም፣... ይዞ (ቢያንስ በየሳይበሩ) መሰለፍ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ውጤታማ ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ አስባለሁ፡፡ አበቃሁ፡፡